# ሊቀ መኳስ ይርጋ

(ከሊማ አበባው ይግዛው)

ሊቀ መኳስ ይርጋ፣ የኪነት ናሙና፣
“አለው አለውና! አለው አለውና!”
በቃ ተከተተ፣ "በማተቡ ፀና።"

  አርባያ፣ በለሣ፣ ሊሞ ወይና ደጋ፣ ጎንደር የበቀለ፣
  አመሉ ከግብሩ፣ ተስተካከለ፣
  የት ነበር? የት አለ? የት አለ?
  መተኪያ የሌለው፣ እንደ ይርጋ ያለ?

ባልረባባ ነገር፣ ልቤ ባልሻከረ፣
ለይርጋ መቀኘት፣ ሙያዬ ነበረ።

  ከጀግኖቹ ጎራ፣ በለሳ በቅለህ፣
  የተከዜን ኮለሽ፣ መናን ጠጥተህ፣
  ገና በጭቅላነት፣ ወኔን ተግተህ፣
  “ እረ ገዳይ!” እንዳልህ፣ ጥቃትን ጠልተህ፣
  ጀግኖችን ቀስቅሰህ፣ እንዳላዘመትህ፣
  አያ ሞት ሰው ጤፉ፣ እንደት ደፈረህ?
  ሊቀ መኳስ ይርጋ፣ ለካ አንተም ሰው ነህ?

ቅኝትህ ሳይለውጥ፣ ድምጽህ እንዳማረ፣
ዝንተ-ዓለም የምትኖር፣ ይመስለን ነበረ!
የማይደቀው ቃልህ፣ ምነው ተሰበረ?
ሊቀ መኳስ ይርጋ፣ "ደሜ! ደሜ! ደሜ!”
ምነው ባልነፈገህ፣ ከማያልቀው ዕድሜ?

  በጎንደሩ ኪነት፣ መድረክ ሲያስተጋባ፣
  ሠርካለም ውቢቱን፣ ያችን ጠይም ለጋ፣
  እንዲያ እንድትሠግር፣ አንገቷ እስኪለጋ፣
  ማነው የገረፋት፣ በመሲንቆ አለንጋ?
  አንገት ከትከሻ፣ ለይታ እንድትመታ?
  ምሳሌ እንድትሆን፣ ለጎንደር እስክስታ?
  ሁዋላም እነንዬን፣ አምሳያ ተክታ፣
  ዓለም ያደነቃት፣ የኪነቱ ዋልታ፣
  ሲያወሱት ደስ ይላል፣ የይርጋን ውለታ።

ዝነኛው፣ ባህላዊው፣ ያ የጎንደር ኪነት፣
ወደ ካራማራ፣ ለድል በዓል ሲዘምት፣
አምስት ቀን ሙሉ፣ በጭንሃክሰን እርሻ፣
አረሙን ስናርም፣ እስከመጨረሻ፣
ይርጋ አልነበረም ወይ፣ የወኔው ወጌሻ?!
በበዓሉም ሆነ፣ ባረሙ ምረቃ፣
የሱ ቅኝት ነበር፣ ለውጤት ያበቃ።

ለሚመለመለው፣ ወዶ ዘማች ሁሉ፣
ለመደበኛውም፣ ሠራዊት በሙሉ፣
ድምፅህ መርፌ ነበር፣ መሰንቆህ ክትባት፣
ወኔን የሚዘራ፣ የድፍረት መዲሃኒት፣
በምሥራቅ፣ በሰሜን፣ በየጦሩ አውድማ፣
ከቶ የት ይገኛል፣ ድምፅህን ያልሰማ?

ሁሉን የሚደፍር፣ ክፉ ባለጌ ሞት፣
“የፍዬል ወጠጤ፣ ትከሻው ያበጠ፣ ልቡ ያበጠበት፣
እንዋጋ ብሎ፣ (ለይርጋ) ላከበት፣
የማትረባ ፍዬል፣ (ሥጋ ለባሽ እናት)፣ ዘጠኝ ትወልዳለች፣
ልጇቿም ያልቃሉ፣ እሷም ትሞታለች።"

ግጥሙንስ አሳካሁ፣ ቅኔው ቤት ሞላልኝ፣
’ጃሎ መገን!” ማን ያንጎራጉርልኝ?
ተነስ አያ ይርጋ! ያንን መሰንቆህን፣ እስኪ ግረፍልኝ!?
መረዋ ድምፅህን፣ በሞቴ ቃኝልኝ፣
ጎርደድ፣ ጎርደድ በል፣ ናፍቆቴ ይውጣልኝ!

ሊቀ መኳስ ይርጋ፣ የቅላፄው መምህር፣
እውን ድምፅህ ጠፋ? ተጫነህ መቃብር?
ድምፅን እንደ ብረት፣ ይበላል ወይ አፈር?
ምንኛ ከንቱ ነው፣ ሰው ሆኖ መፈጠር?
ጎበዝ በያ’ፉፉ፣ ጬኸ ጥና ጥሩ፣
ለጭህራ ንገሩ፣
ለጠዳ ንገሩ፣
ለሁሉም ንገሩ፣
ይርጋ፣ ይርጋ ሲባል፣ ተጫነው አፈሩ።

"አለው አለውና!” አያ ይርጋ አረፈው?!
ሻምበል መሰንቆውን፣ ደጋግመህ ግረፈው፣
ሁሉንም የምትጠቅስ፣ መቃብር ደፋሯ፣ ወይዘሮ ጠለሉ፣
ይርጋን በሰማንያ፣ አገባችው አሉ?!

ይርጋ በዋልክበት፣ ለዋሉት በሙሉ፣
አብረውህ ለጠጡ፣ አብረውህ ለበሉ፣
ለኪነቱ አባላት፣ ለነታማኝ ሁሉ፣
አያ ይርጋ ሞተ፣ የሚባለው መርዶ፣
እንደት ይጫናቸው፣ እንደ ድንጋይ ከብዶ?

ስማኝ አያ ይርጋ! እኒያ እምታውቃቸው፣
በጣም የሳሱልህ፣ እንዳ’ይን ብሌናቸው፣
ሁሉንም ባሉበት፣ ጥናቱን ይስጣቸው።



EthioLion.com